**<u>ቅጽ 4</u>**

(ክፍል 112(1))

**<u>የእርስዎን የውሃ አቅርቦት ለማቋረጥ ከውሃ ባለስልጣን ዳይሬክተር ፈቃድ እንዲሰጠን ጥያቄ ለማቅረብ ማቀዳችንን ስለማሳወቅ</u>**

**የውሃ አቅርቦት ከመቋረጡ በፊት የሚሰጥ ማስጠንቀቂያ**

**የውሃና ፍሳሽ ኮርፖሬሽን ደንቦች (የውሃ አቅርቦት ወይም የፍሳሽ አገልግሎት ማቋረጥ)፤ 5775-2015**

1. በ ________________________________ ለሚገኘው ንብረትዎ ለ ________________________ ወር ለቀረበልዎ የውሃ ወይም ፍሳሽ አግልግሎት መክፈል ያለበዎትን ሂሳብ ለድርጅቱ እንዲከፍሉ ማስጠንቀቂያና ማሳወቂያ የተላከለዎት ቢሆንም እስካሁን አለመክፈልዎትን መረጃዎቻችን ያሳያሉ፤ ይህ ደብዳቤ በተጻፈልዎት ቀን ለድርጅቱ መክፈል ያለብዎትውዝፍ ዕዳ ________ NIS የደረሰ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ________ NIS ዕዳ ሲሆን (ከዚህ በኋላ "ወቅታዊ ዕዳ" እየተባለ የሚጠራው) ይህም ዕዳ ሙሉ በሙሉ ተከፍሎ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ውዝፍ እየተጠራቀመ የሚሄድ ነው፡፡

2. የውሃ ባለስልጣን ዳይሬክተር መ/ቤታቸው ለእርስዎ ንብረት የሚያቀርበውን የውሃ አገልግሎት እንዲያቋርጥ ጥያቄ ለማቅረብ የተዘጋጀን ሲሆን ከጥያቄያችን ጋርም እርስዎን የሚመለከቱ ሰነዶችን አያይዘን እናቀርባለን፡፡ እርስዎም ለእኛ ለማቅረብ የሚፈልጓቸውን ሰነዶች ጭምር (ከዚህ በኋላ በአንቀጽ 8 ላይ እንደተገለጸው) እናቀርባለን፤

3. ጥያቄያችንን ለውሃ ባለስለጣን ዳይሬክተር ከማቅረባችን በፊት ከዚህ ደብዳቤ ጋር በተያያዘው የክፍያ ስሊፕ መሰረት ወቅታዊ ዕዳዎትን ባስቸኳይ ከፍለው እንዲያጠናቅቁ በድጋሚ እንጠይቃለን፤ ክፍያው በየትኛውም የፖስታል ባንክ/ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ/በቴሌፎን መልስ መስጫ አገልግሎት በኩል በክሬዲት ካርድ/በኮርፖሬሽኑ ድረ ገጽ በኦንላይን መክፈል ይቻላል፡፡

4. አሁን ያለብዎትን ዕዳ ባፋጣኝ ሳይከፍሉ ከቀሩ፣ የውሃ ባለስልጣን አማካሪ ኮሚቴ ለንብረትዎ የሚቀርበው የውሃ አገልግሎት እንዲቋረጥ የማድረግ እርምጃ እንዲወሰድ ለውሃ ባለስልጣን ዳይሬክተር የውሳኔ ሃሳብ ሊያቀርብ የሚችል ሲሆን ይህ መደረጉ ግን እኛ ከእርስዎ ማግኘት የሚገባንን የአገልግሎት ሂሳብ ለመቀበል የሚያስችሉንን ማናቸውም እርምጃዎች ከመውሰድ አያግደንም፤ ለምሳሌም በታክስ ሕግ (አሰባሰብ) ወይም በአፈጻጸም ሕግ 5727-1967 መሰረት የተሰጠንን ስልጣን መተግበርና የባንክ ሂሳብዎን ወይም ሌሎች ንብረቶችዎን ማሳገድ እንችላለን፡፡

5. ለንብረትዎ የሚቀርበው የውሃ አገልግሎት መቋረጡ የተለያዩ ወጪዎችን እንደሚያስከትልብዎ በአጽንኦት ለማሳወቅ እንፈልጋለን፤ ለምሳሌም እነዚህ እርምጃዎች ተግባራዊ ከተደረጉ፣ የአገልግሎት መስመር ማቋረጫና ማስቀጠያ ክፍያ በውሃና ፍሳሽ ኮርፖሬሽን ደንብ 5770-2009 ሁለተኛ ሰንጠረዥ ተ.ቁ. 3 እና 5 ላይ በተገለጸው መሰረት (የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት እና የውሃ ወይም ፍሳሽ ሲስተም ዝርጋታ ወጪ) መክፈል ይጠበቅብዎታል፡፡

6. ዕዳዎን በተለያየ ጊዜ ከፍለው ለማጠናቀቅ መስማማት ከፈለጉ፣ እባክዎ ለደንበኞች አገልግሎት ማዕከላችን በስልክ ቁጥር ____________ ደውለው ያሳውቁ ወይም በ _____________ አድራሻ ይጻፉልን፡፡

7. **ዕዳዎን ለድርጅቱ ለመክፈል የሚያስችል አቅም ከሌለዎት ወይም ድርጅቱ ገንዘቡን ለመሰበሰብ እንዲያስችለው መረጃ ለመስጠት ከፈለጉ፣ የውሃ አቅርቦትዎ እንዲቋረጥ ለውሃ ባለስልጣን ዳይሬክተር ልናቀርበው የነበረውን ጥያቄ እንድናቆም ይህ ደብዳቤ በደረሰዎ በ21 ቀናት ውስጥ ድርጅቱን መጠየቅ ይችላሉ፤ ጥያቄዎ ተቀባይነት ሊያገኝ ወይም ላያገኝ የሚችለው በድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ውሳኔ መሰረት ነው፡፡**

8. **ጥያቄዎን ለማቅረብ ከዚህ ጋር የተያያዘውን ቅጽ መጠቀም የሚችሉ ሲሆን የፋይናንስ ሁኔታዎን ጨምሮ የጥያቄዎን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ፣ በእጅዎ የሚገኝ ማንኛውም ደጋፊ ሰነድ ወይም መረጃ ከጥያቄዎ ጋር አያይዘው ማቅረብ ይችላሉ፤ ይህን መረጃ በቀጥታ ለውሃ ባለስልጣን አማካሪ ኮሚቴ ለማስተላለፍ ከፈለጉ፣ ጥያቄዎን ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን ለዚህ ተግባራዊነት ግን የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ የውሃ አቅርቦት ማቋረጫ ጥያቄ ለማቅረብ መወሰን አለባቸው፡፡**

**ለመረጃ እንዲሆንዎ፡**

✓ ከላይ እንደተገለጸው፣ ጥያቄያችንን ለባለስልጣኑ ዳይሬክተር ለማቅረብ መወሰናችንን ለማሳወቅ ለአካባቢው መንግስት የማሕበራዊ አገልግሎት መምሪያ (ከዚህ በኋላ "የማሕበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ") ለማሳወቅና እርስዎም በእነርሱ ዘንድ የሚታወቁ መሆንዎትን የሚያረጋግጥ ደብዳቤና የእርስዎን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የሚመለከቱ ማናቸውም መረጃዎችን በተጠየቁ በ21 ቀናት ውስጥ እንዲልኩልን ለመጠየቅ አቅደናል፤

✓ ይህ ማስታወቂያ የደረስዎ መሆኑን በ7 ቀናት ውስጥ ካላሳወቁን፣ ከላይ የተገለጸውን ጥያቄ እንዳልተቀበሉት ይቆጠራል፤

✓ በታክስ ሕግ (አሰባሰብ)፣ በአፈጻጸም ሕግ 5727-1967 መሰረት እርምጃ መወሰዱ ወይም የውሃ አቅርቦት መቋረጡ ለድርጅቱ መክፈል ያለብዎን ሙሉ ዕዳ ከመክፈል ነጻ አያደርግዎትም፤

✓ ከላይ የተጠቀሱት እርምጃዎች ቢወሰዱም እንኳን ሙሉ ዕዳው ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ዕዳዎ ወለድና ቅጣት እያጠራቀመ ይሄዳል፤

✓ መከራከሪያ ሃሳብዎን በቃልም ሆነ በጽሁፍ ለድርጅቱ ማቅረብ ይችላሉ፤

✓ በእርስዎ ጉዳይ ላይ ዋና ስራ አስኪያጁ ውሳኔ የሚወስኑት በተሰጠዎት የጊዜ ገደብ ውስጥ ያቀረቧቸውን መከራከሪያዎችና መረጃዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

ቀደም ሲል ዕዳዎን ከፍለው ያጠናቀቁ ከሆነ፣ ይህን ማስታወቂያ እንደማያገለግል ይቁጠሩት፡፡

**ቅጽ 5**

(ክፍል 112(2))

**በተለይ ለ**

**ውሃና ፍሳሽ ኮርፖሬሽን**

**Re:** **<u>በውሃና ፍሳሽ ኮርፖሬሽን ደንብ 5775-2015 (የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት መቋረጥ) መሰረት ለንብረቱ ይቀርብ የነበረው የውሃ አቅርቦት እንዲቋረጥ የተዘጋጀው ጥያቄ ለውሃ ባለስልጣን ዳይሬክተር እንዳይተላለፍ ስለመጠየቅ</u>**

ከድርጅታችሁ በደረሰኝ ማሳወቂያና ለእናንተ መክፈል ባለብኝ ዕዳ መሰረት ፣ ከዚህ በታች በዘረዘርኳቸው ምክንያቶች የተነሳ ለንብረቱ ይቀርብ የነበረው የውሃ አቅርቦት እንዲቋረጥ የተዘጋጀው ጥያቄ ለውሃ ባለስልጣን ዳይሬክተር እንዳይተላለፍ እጠይቃለሁ፡

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

ከዚህ ጋር የተያያዙት ሰነዶች የእኔን (ወይም በንብረቱ ውስጥ አብረውኝ የሚኖሩትን የቤተሰብ አባላቶቼን) የጤና/ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የሚያረጋግጡ ናቸው

☐ የእኔን (ወይም በንብረቱ ውስጥ አብረውኝ የሚኖሩትን የቤተሰብ አባላቶቼን) የጤና/ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የሚያረጋግጡ ሰነዶችን ለድርጅቱ ለማቅረብ አላሰብኩም፡፡

☐ የድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ በአማካሪ ኮሚቴው በኩል የእኔን ጉዳይ በተመለከተ ጥያቄውን ለውሃ ባለስልጣን ዳይሬክተሩ ለማቅረብ ከወሰኑ፣ የእኔን (ወይም በንብረቱ ውስጥ አብረውኝ የሚኖሩትን የቤተሰብ አባላቶቼን) የጤና/ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የሚያረጋግጡ ሰነዶችን በቀጥታ ለውሃ ባለስልጣን አማካሪ ኮሚቴ ለማቅረብ እፈልጋለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር፣

መጠሪያ ስም + የአያት ስም

ንብረቱ የሚገኝበት አድራሻ

የደንበኛው የግንኙነት አድራሻ <u>(ካስፈለገ)</u>-

የኢሜይል አድራሻ፡

ስልክ ቁጥር፡

ሞባይል ስልክ ቁጥር፡

**ቅጽ 6**

(ክፍል 112(6))

**በተለይ ለ**

**<u>የደንበኛው ስምና አድራሻ</u>**

**<u>በውሃና ፍሳሽ ኮርፖሬሽን ደንብ 5775-2015 (የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት መቋረጥ) አንቀጽ 6(a)(8) መሰረት የዋና ስራ አስኪያጁን ውሳኔ ስለማሳወቅ</u>**

(1) <u>በላክንልዎ ማስጠንቀቂያና ማሳወቂያ መሰረት እንደዚሁም እርስዎ ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት፣ የውሃ ባለስልጣን ዳይሬክተር ለንብረትዎ ይቀርብ የነበረውን የውሃ አገልግሎት እንዲቋረጥ ፈቃድ ይሰጡን ዘንድ ለመጠየቅ ወስኛለሁ::</u>

(2) <u>ውሳኔዬም በሚከተሉት ምክንያቶች ላይ የተመሰረተ ነው፡</u>

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

<u>ለመረጃ እንዲሆንዎ፡</u>

- ✓ <u>የውሃ ባለስልጣን አማካሪ ኮሚቴ በበውሃና ፍሳሽ ኮርፖሬሽን ደንብ 5775-2015 (የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት መቋረጥ) አንቀጽ 8 መሰረት የተቋቋመ ኮሚቴ ነው::</u>
- ✓ የኮሚቴው ተግባር ድርጅቶች የአገር ውስጥ ደንበኞችን የውሃ አቅርቦት እንዲቋረጥ በሚያቀርቡት ጥያቄ ላይ ተወያይቶ ጥያቄዎቹን እንዲቀበል፣ እንዳይቀበል ወይም በማሻሻያ እንዲቀበል ለውሃ ባለስልጣን ዳይሬክተሩ ሃሳብ ማቅረብ ነው:: .
- ✓ ለውሃ ባለስልጣን አማካሪ ኮሚቴው በቀጥታ መጻፍ የሚችሉ ሲሆን ጉዳዩን የሚመለከቱ ማናቸውንም ሰነዶች ማቅረብም ይችላሉ::
- ✓ የኮሚቴው መገኛ አድራሻ፡ ________________________

ከሰላምታ ጋር፣

መጠሪያ ስም + የአያት ስም

<u>የ__________ ኮርፖሬሽን ዋና ስራ አስኪያጅ</u>

**ቅጽ 8**

**(ክፍል 115)**

**በውሃና ፍሳሽ ኮርፖሬሽን ደንብ 5775-2015 (የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት መቋረጥ) አንቀጽ 14 መሰረት የተሰጠ የአገልግሎት ማቋረጫ ማስታወቂያ**

1. የውሃ ባለስልጣን ዳይሬክተሩ በእርስዎ ጉዳይ ላይ ከአማካሪ ኮሚቴው የቀረበላቸውን የውሳኔ ሃሳብ ለመቀበልና ለእርስዎ ንብረት ይቀርብ የነበረውን የውሃ አገልግሎት ለማቋረጥ እንዲችል ፈቃድ ለመስጠት በቀን _______ ወስነዋል፡፡

2. የውሃ ባለስልጣን ዳይሬክተሩን ውሳኔ ለመቃወም በከፍተኛው ፍ/ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

3. **ማስታወሻ፡ ይህ ማስታወቂያ ከደረሰዎ በኋለ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለንብረትዎ ሲቀርብ የነበረውን ውሃ አገልግሎት ለማቋረጥ አቅደናል፡፡**
   **ለ30 ተከታታይ ቀናት የውሃው አቅርቦት ተቋርጦ የሚቆይ ሲሆን ከዚያ በኋላ ለ5 ተከታታይ ቀናት መስመሩን እንደገና በመቀጠል ለእኛ መክፈል ያለብዎትን ዕዳ እንዲከፍሉ እድል እንሰጥዎታለን፡፡**

4. **ከላይ እንደተገለጸው ዕዳዎትን በ5 የስራ ቀናት ውስጥ ካልከፈሉ፣ ድርጅቱ ረዘም ላለ ጊዜ የውሃ አገልግሎቱን ማቋረጡን ሊቀጥል የሚችል ሲሆን ከእርስዎ መሰብሰብ የሚገባውን ገንዘብ ለመቀበል በውሃና ፍሳሽ ኮርፖሬሽን ደንብ 5775-2015 (የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት መቋረጥ) መሰረት ማንኛውንም መንገድ ሊጠቀም ይችላል፡፡**

**ለመረጃ እንዲሆንዎ፡**

✓ የውሃ መስመሩ ከመቋረጡ ቢያንስ 15 ቀናት በፊት በአካባቢያችን ለሚገኘው የማሕበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ የውሃው አገልግሎት ሊቋረጥ እንደሚችል እናሳውቃለን፡፡

✓ ይህ ደብዳቤ ወጪ በሆነበት ቀን ለድርጅቱ መክፈል ያለብዎ ዕዳ መጠን __________ NIS ሲሆን ሙሉ በሙሉ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስም ወለዱ እየተጠራቀመ ይሄዳል፡፡

✓ የውሃ አቅርቦቱ እንዳይቋረጥ ለማድረግ ከፈለጉ ዕዳዎን በአፋጣኝ መክፈል ያለብዎ ሲሆን ክፍያውን ከዚህ ጋር በተያያዘው የክፍያ ስሊፕ መሰረት በየትኛውም የፖስታል ባንክ/ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ/በቴሌፎን መልስ መስጫ አገልግሎት በኩል በክሬዲት ካርድ/በኮርፖሬሽኑ ድረ ገጽ በኦንላይን መክፈል ይቻላል፡፡

- ✓ **በተመሳሳይም፣ የውሃ አገልግሎት ከተቋረጠና እነዚህ እርምጃዎችም ተግባራዊ ቢደረጉ የአገልግሎት መስመር ማቋረጫና ማስቀጠያ ክፍያ** በውሃና ፍሳሽ ኮርፖሬሽን ደንብ 5770-2009 ሁለተኛ ሰንጠረዥ ተ.ቁ. 3 እና 5 ላይ በተገለጸው መሰረት (የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት እና የውሃ ወይም ፍሳሽ ሲስተም ዝርጋታ ወጪ) መክፈል ይጠበቅብዎታል።
- ✓ ዕዳዎን በተለያየ ጊዜ ከፍለው ለማጠናቀቅ መስማማት ከፈለጉ፣ እባክዎ ለደንበኞች አገልግሎት ማዕከላችን በስልክ ቁጥር ____________ ደውለው ያሳውቁ ወይም በ _____________ አድራሻ ይጻፉልን።

**ቅጽ 9**

(ክፍል 116)

**ዕዳ ባለመከፈሉ ምክንያት የውሃ አቅርቦት ከመቋረጡ በፊት በውሃና ፍሳሽ ኮርፖሬሽን ደንብ 5775-2015 (የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት መቋረጥ) አንቀጽ 18 (c) እና (d) መሰረት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ**

ለእኛ መክፈል ያለብዎትን ዕዳ ባለመክፈልዎ ምክንት በ ______________ ለሚገኘው ንብረትዎ ይቀርብ የነበረውን የውሃ አቅርቦት በቀን ________________ እንዲቋረጥ አድርገናል፡፡

ዕዳዎትን ከፍለው ያልጨረሱ ቢሆንም እንኳን ከ ___________ ጀምሮ ለ5 የስራ ቀናት ለጊዜው  መስመሩን መልሰን የቀጠልን ሲሆን በዚህ ጊዜ ውስጥ መስመሩን ለመቋረጥ ያበቃውን ወቅታዊ ዕዳ ለድርጅቱ ከፍለው ማጠናቀቅ ነበረብዎት፡፡

ይህ ደብዳቤ ወጪ በሆነበት ቀን ለድርጅቱ መክፈል ያለብዎ ዕዳ መጠን __________ NIS ሲሆን ሙሉ በሙሉ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስም ወለዱ እየተጠራቀመ ይሄዳል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘው የክፍያ ስሊፕ አማካይነት ዕዳዎን በአስቸኳይ ከፍለው እንዲያጠናቅቁ እንጠይቃለን፡፡

**ከላይ እንደተገለጸው ዕዳዎትን በ5 የስራ ቀናት ውስጥ ካልከፈሉ፣ ድርጅቱ ረዘም ላለ ጊዜ የውሃ አገልግሎቱን ማቋረጡን ሊቀጥል የሚችል ሲሆን  ከእርስዎ መሰብሰብ የሚገባውን ገንዘብ ለመቀበል በውሃና ፍሳሽ ኮርፖሬሽን ደንብ 5775-2015 (የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት መቋረጥ) መሰረት ማንኛውንም መንገድ ሊጠቀም ይችላል፡፡**

**ለመረጃ እንዲሆንዎ፣ የውሃ አገልግሎት ከተቋረጠና እነዚህ እርምጃዎችም ተግባራዊ ቢደረጉ የአገልግሎት መስመር ማቋረጫና ማስቀጠያ ክፍያ** በውሃና ፍሳሽ ኮርፖሬሽን ደንብ 5770-2009 ሁለተኛ ሰንጠረዥ ተ.ቁ. 3 እና 5 ላይ በተገለጸው መሰረት (የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት እና የውሃ ወይም ፍሳሽ ሲስተም ዝርጋታ ወጪ) መክፈል ይጠበቅብዎታል፡፡

**ከዚህ በኋላ ተጨማሪ ማስጠንቀቂያ አይላክም!**